የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.41
ADDIS ABABA 22th June, 2022

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸/፪ሺ፲፬

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተፈረመው የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ.....................................ገጽ ፲፬ሺ፫፻፮

## Content

Proclamation No. 1270/2022

Military Financial Cooperation Agreement Between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey Ratification Proclamation ………..Page 14306

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸/፪ሺ፲፬**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት ለማጸደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም. በአንካራ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህኑን ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO. 1270 /2022**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE MILITARY FINANCIAL COOPERATION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKEY**

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey have signed a Military Financial Cooperation Agreement on 18th of August 2021 in Ankara;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on 17th Day of May, 2022;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተፈረመው የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም. በአንካራ የተፈረመው የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Military Financial Cooperation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey Ratification Proclamation No.1270/2022".

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Military Financial Cooperation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey, signed on 18th August in Ankara, is hereby ratified.

## 3. <u>Implementing Organ</u>

The Ministry of Defense of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this Day of June 22th 2022.**

**SAHALE - WORK ZEWEDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**